focus on facts

# የማኒቶባ ሰራተኞች የስራ ቦታ ጤናና ደህንነት መብት

## የጤናና ደህንነት ሕግ

በካናዳ የሰራተኛ ማህበራት ድንጋጌና በማኒቶባ የሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት ደንብ መሰረት ተቀጣሪዎች በሥራ ቦታ ዙሪያ ያላቸው ደህንነትና ጤንነት መብት የተረጋገጠ ነው። ይህ በራሪ ወረቀት በማኒቶባ የሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት ደንብ ላይ የሰፈሩ የተቀጣሪ መብቶችን በዝርዝር ያስቀምጣል ።

አብዛኛዎቹ ተቀጣሪዎች በማኒቶባ የስራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት ደንብ መብቶቻቸው ይጠበቃል። በፌደራል መንግስት ስር በአገልግሎትሰጪ መንግስት ኮርፖሬሽኖች በባንኮች በመጓጓዣ ድርጅቶችና በህዝብ ግንኙነት ተቋሚት ተቀጣሪዎች፥ እንዲሁም የእህልና ጥራጥሬ ኢንዱስትሪ ተቀጣሪዎች መብት በካናዳ የሠራተኞች ማህበር ህግ መሰረት የተጠበቀ ይሆናል።.

የካናዳ የሰራተኞች ማህበራት ድንጋጌና የማኒቶባ የሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት ደንብ በሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት ዙሪያ ያላቸው ሕግ ተመሳሳይ ነው ። በካናዳ የሰራትኛ ማህበር አዋጅ ጥላ ስር የሚተዳደሩ ሰራተኞች ግን በሥራ ቦታ ዙሪያ ያላቸውን ደህ ንነት መብት አስመልክቶ የሰራተኛ ማህበራቸውን ወይም የካናዳ ሂውማን ሪሶርስ ዴቨሎፕመንትን ማነጋገር ይችላሉ ።

## የሰራተኞች የጤንነትና የደህንነት መብቶች

### የማወቅ መብት

ሰራተኞች በሥራ ቦታቸው ላይ ስላሉ ጎጂ ነገሮች የማወቅ መብት አላቸው። ሰራተኞች በሥራ ገበታቸው ዙሪያ ሊደርስባቸው ስለሚችለው ጉዳት ማሳወቅና ራሳቸውን ካደጋ ጠብቀው መስራት የሚያስችለውን ስልጠና ቀጣሪዎች እንዲሰጡ ሕግ ያስገድዳቸዋል።

በተጨማሪም የጎጂ መገልገያዎች መረጃ ልውውጥ (WHMIS) ተብሎ የሚጠራው የጤናና ደህንነት ጥበቃ ዘዴ የሰራተኞችን ደህንነት ይጠብቃል ። በዚህ ዘዴ መሰረትም ቀጣሪዎች የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች እንዲያሟሉ ይጠይቃል :-

- ጎጂነት ያላቸው ነገሮች መያዣ (ማስቀመጫ ) እቃዎች የጽሑፍ ምልክት እንዲደረግባቸው
- የመገልገያ መሳሪያዎች ፅሁፋዊ መረጃ (MSDS) ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ
- ስለጎጅ መገልገያዎች ስለ አጠቃቀማቸውና ሰራተኞች እንዴት አራሳቸውን መጠበቅ እንደሚችሉ የሚያስረዳው የስልጠናና አጠቃቀም ዘዴ እንዲያቀርብ ይጠበቃል ።

የመገልገያ መሳሪያው ደህነንት ፅሁፋዊ መረጃ ተዘጋጅቶ መቅረብ ያለበት በአምራቹ ኩባንያና በአከፋፋዩ ሲሆን መሳሪያው ከምን እንደተሰራ ንጥረ ነገሩ የተዘጋጀበትን ጥሬ እቃና የጤና ጠ ንቆቹ ምን እንደሆኑ እንዲሁም መወሰድ ያለባቸውን ጥንቃቄዎች ዝርዝር የያዘ ነው። ይህ ፅሁፋዊ መረጃ በሥራ ቦታ ተቀምጦ ሰራተኞች እንዲጠቀሙበት ይደረጋል ።

### የተሳትፎ መብት

በሥራ ቦታ ጤንነትና ደህንነትን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ሰራተኞች የመሳተፍ መብት አላቸው። ሰራተኞች የስራ ቦታ ጤንነትና ደህንነትን አስመልክቶ የተሰማቸውን ቅሬታ በድርጅቶቻቸው ለሚገኙ የስራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት ኮሚቴዎች ወይም ለስራ ቦታ ጤነንትና ደህንነት ተወካዮች ማቅረብ ይችላሉ።

### የጤናና ደህንነት ኮሚቴዎች

ሃያና ከዚያ በላይ ሰራተኞች ያሉበት ማንኛውም ቀጣሪ ድርጅት ቀጣሪ ና ተቀጣሪን አጠቃሎ ያቀፈ የስራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት ኮሚቴ መመስረት አለበት። በዚሁ ኮሚቴ ውስጥ ያሉት አባላት ቢያንስ ቢያንስ ግማሽ የሚሆኑት ከሰራተኛው ወገን የተውጣጡ መሆን አለባቸው።

### የኮሚቴው ተሳትፎ

ሰራተኞች ወኪሎቻቸውን የመወሰን መብት አላቸው። የሰራተኛ ተወካዮች የሚመረጡት በሁለት መንገድ ሲሆን ይህም በባልደረቦቻቸው ወይም ደግሞ በሰራተኞች ማህበር አማካኝነት ነው። የኮሚቴው አባላት ስም ዝርዝር በመስሪያ ቤቱ ግልፅና በሚታይ ቦታ ላይ በቁዋሚነት መለጠፍ አለበት ።

### የኮሚቴው የስራ ድርሻዎች

ከአስሪና ሰራተኛ የተውጣጡ ጥምር የስራ ቦታ ጤና ደህንነት ኮሚቴ አባላት ቢያንስ በሶስት ወር ውስጥ አንዴ መሰብሰብ አለባቸው ። ኮሚቴው የስራ ቦታ ደህንነትና ጤናን ሁኔታ ይገመግማል አደጋዎችን ይመረምራል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ግምገማ ያለማካሄድ መብትን ያስከብራል አሳሳቢ የጤናና ደህንነት ጉዳዮችን ከተለያዩ የስራ ክፍል ባልደረቦች ጋር ይመክራል።

የስራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት ኮሚቴ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ከመደበኛ ስራ ግዜአቸው ፍቃድ ይሰጣቸዋል በዚህም ወቅት የመደበኛ ደሞዛቸው ክፍያ ሳያቅዋርጥ ይቀጥላል

ሰራተኞች በጤናና ደህንነት ዙሪያ ተያይዞ ሊነሳ ስለሚችለው አሳሳቢ ሁኔታ ለተወካዮቻቸው ማሳወቁ ጠቃሚ ነው ።

### የኮሚቴው ስልጠና

የሰራተኞች ተወካዮች ክፍያቸው ሳይጉዋደል በዓመት ለ አስራስድስት ሰዓታት ለሥራ ቦታ ጤናና ደህንነት ሥልጠና ተግባር እንዲሄዱ ቀጣሪዎች የመፍቀድ ግዴታ አለባቸው። ከአምስት ስከ አስራዘጠኝ ሰራተኞች የሚገኙበት ቀጣሪ ድርጅት; የስራ ቦታ ጤናና ደህንነት ተወካዮች ሊኖሩት ግዴታ ነው ። ተወካዮቹም በሥራ ባልደረቦቻቸው ወይም በሰራተኛ ማህበሩ ሊሰየሙ ይችላሉ። ተመራጮቹም ባስተዳደራዊ ሥራ ላይ ያልተሰማሩ መሆን አለባቸው።

የኮሚቴው አባላት ስም ዝርዝር በመስሪያ ቤቱ ግልፅና በሚታይ ቦታ ላይ በቁዋሚነት መለጠፍ አለበት ።

OHC
MFL Occupational Health Centre
Published by the MFL Occupational Health Centre • 102-275 Broadway • Winnipeg, MB • R3C 4M6 • 204-949-0811
UNION UFCW LABEL LOCAL CANADA 832

የሥራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት ተወካይ የስራ ድርሻ ከጤናና ደህንነት ኮሚቴ ሥራ ድርሻ ጋር ይመሳሰላል ::

## የተቃውሞ መብት

ሰራተኞች አንድ ሥራ በራሳቸው በሥራ ባልደረቦቻቸው ወይንም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ከተገነዘቡ ሥራውን የመቃወም መብት አላቸው ::

ይህንኑ ተቃውሞ ለማቅረብ ሰራተኞቹ መከተል ያለባቸው አራት **ደረጃዎች** አሉ ; እነኚህን አራት ደረጃዎች ከተከተሉ ሰራተኞች ሥራውን በመቃወማቸው ወይም ባለመስራታቸው ከስራ አይታገዱም ; አይባረሩም ወይንም ሌላ ቅጣት አይደርስባቸውም:: ደረጃዎቹም እንደሚከተሉት ይሆናሉ :-

**ደረጃ 1** ሰራተኛው ስራውን ለመስራት ያልፈለገበትንና ስጋቱን ለቅርብ አለቃው (.Supervisor) ማሳወቅ

**ደረጃ 2** ቀጣሪው ባስቸከዋይ እርማት ማድረግ ካልቻለ አሰሪው የኮሜቴው ም/ሊቀመንበር እና ተቃውሞውን ያቀረበው ሠራተኛ አንድ ላይ ሆነው ጉዳዩን ባንድ ላይ መመርመር አለባቸው:: በዚህ ወቅት ቀጣሪው ሰራተኛውን በሌላ ሥራ ላይ እንዴመደብ የመጠየቅ መብት አለው ::

አሰሪው ችግሩን ባይፈታም ወይንም ሥራው ጉዳት የለበትም ብሎ ቢወስን እንከዋን ሰራተኛው ተቃውሞውን የመቀጠል መብት አለው::

ቀጣሪው በአንድ ተቀጣሪ ለጤንነትና ደህንነት አስጊ ለመሆኑ ተቃውሞ በቀረበበት የስራ ቦታ ላይ ሌላውን ተቀጣሪ እንዲሰራ መጠየቅ የሚችለው ለግለሰቡ የተቃውሞውን መንስዔ፥ የተቃውሞ መብቱንና የስራ ቦታው ለጤንነትና ደህንነት የማያሰጋ መሆኑን በመግለፅ በፅሁፍ ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል::

**ደረጃ** 3 ስለስራው በቂ ግምገማ ከተደረገ በህዋላ ችግሩ አሁንም ካልተፈታ ሰራተኛው ቀጣሪው ወይንም የኮሚቴው ምክትል ሊ/መንበር የማኒቶባ የስራ ቦታ ጤናና ደህንነትን ቅርንጫፍ መ/ቤት በመጥራት ስለተቃውሞና ስለምክንያቱ ማስረዳት አለባቸው::

**ደረጃ** 4 የሥራ ቦታ ጤናና ደህንነት ተወካይ ከሰራተኛው ከቀጣሪው ወይንም የኮሚቴው ም/ሌቀመንበር በተገኙበት ጉዳዩን አጣርቶ ይመረምራል ; ስራው አደገኛ መሆኑን ካመነበት ቀጣሪው እንዲያስተካክለው የሚያዝ ሪፖርት ይፅፋል የስራውን አደገኛነት ካላመነበት ግን ሰራተኛው ወደ ሥራው እንዲመለስ ያዛል (ይወስናል)::

ደህንነትን የመጠበቅ መብት

ተቀጣሪዎች በተመደቡባቸው የስራ መስኮች ላይ ጤንነትና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የተለያዩ እርምጃዎች የመውሰድ መብታቸው የተጠበቀ ነው:: እነዚህንም መብቶች ለማስጠበቅ በሚወስዷቸው እርምጃዎች ምክንያት ምንም ዓይነት ቅጣት ሊደርስባችው አይችልም:: ለዚህም ጤንነትና ደህንነታቸውን አደጋ ላይ የሚጥል ስራን አልሰራም ማለት፥ስጋታቸውንም ሆነ ቅሬታቸውን ለሚመለከተው ክፍል የማቅረብና የመደበኛ ክፍያቸው ሳይቅረጥ በስራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት ኮሚቴዎች ውስጥ የሚሳተፉበት ፈቃድ የማግኘት መብቶቻቸው የተጠበቁ ይሆናሉ::

ነገር ግን ተቀጣሪዎች ያለአግባብ ቅጣት እንደደረሰባቸው ካመኑ፥ ቅሬታቸውን ለስራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ማቅረብ ይችላሉ:: የቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ ተወካይም ቅሬታውን ተቀበሎ ጉዳዮን ያጣራል:: ጉዳዮ ተጣርቶ ተፈፀመ የተባለው በደል ከተረጋገጠ፥ የቅርንጫፍ ተወካዮ በቀጣሪው ላይ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ሊያስተላልፍ ይችላል፥፥ እነዚህም፥ ቀጣሪው

- የመድልዎ ድርጊቱን በአስቸኳይ እንዲያቆም
- ለተቀጣሪው ያላግባብ ያጣውን ደሞዝና የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከፍል
- በተቀጣሪው ላይ የተጣሉ ዕገዳዎችንም ሆኑ ቅጣቶችን እንዲሰርዝ
- ለተቀጣሪው ከ ፩ ሺህ እስከ ፲ ሺህ የሚደርስ መቀጮ እንዲከፍል ሊያደርግ ይችላል::

ይግባኝ

ቀጣሪው ወይም ተቀጣሪው በተላለፈው ውሳኔ ላይ ቅር ከተሰኙ፥ ይህንኑ ተቋሚቸውን ውሳኔው በተላለፈ አስራ ዓራት ቀናት ውስጥ ለቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ::

**ለተጨማሪ መረጃ**

የስራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ስልክ ቁጥር 204-957-SAFE (7233) ወይም 1-855-957-SAFE.

ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች

## Regional Offices

**Winnipeg**
200-401 York Ave
Winnipeg, MB
R3C 0P8

**Brandon**
340 9th St.
Brandon, MB
R7A 6C2

**Flin Flon**
202-143 Main Street
Flin Flon, MB
R8A 1K2

**Thompson**
59 Elizabeth Drive
Thompson, MB
R8N 1X4

**Human Resources Development Canada**
**Labour Program**
2nd Floor, 391 York Avenue
Winnipeg, Manitoba R3C 0P8
Ph: 204-983-6375

Revised April 2017
Amharic - Workers Rights